በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

Federal Democratic Republic of Ethiopia
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

መስከረም 16 ቀን 2013 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# 90ኛ መደበኛ የካቢኔ ዉሳኔዎች

የሚኒስትሮች ም/ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 90ኛ መደበኛ ስብሰባ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳለፈ፡፡

1. በመጀመሪያ ምክር ቤቱ የተወያየው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርዓት እና የማስረጃ ህግ ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው፡፡ በስራ ላይ ያለው የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስነስርዓት በ1954 ዓም የታወጀና አሃዳዊ የመንግስት አወቃቀርና አስተዳደር ስርዓትን የተከተለ በመሆኑ የምንተገብረውን የፌደራል ስርዓትና በክልልና በፌደራል መንግስታት መካከል ያለውን ህግ መንግስታዊ የስልጣን ክፍፍል ያላገናዘበ በመሆኑ እንዲሁም አገራችን በርካታ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶችን በተለይም የሲቪልና የፖለቲካል መብቶች፣ የሕጻናት መብቶች፣ ሴቶች መብቶች እና ሌሎች መብቶችን የተመለከቱ አለም አቀፍና አሕጉራዊ ስምምነቶችን ተቀብላ የአገሪቱ ህግ አካል ያደረገቻቸው በመሆኑ እነዚህን ለውጦች ያገናዘበ እና በስራ ላይ ካሉ ህጎች ጋር የሚጣጣም ለውጥ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ በሌላም በኩል በስራ ላይ ያለው የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርአት ህግ በበርካታ ጉዳዮች ላይ ግልፅነት የጎደለው፣ ዛሬ ላይ ከሚፈጸሙ ውስብስብና የረቀቁ ወንጀሎች አንጻር እንዲሁም ዘመኑ ከደረሰበት የወንጀል ሳይንስ ጋር አብረው የማይሄዱ በርካታ ድንጋጌዎች የተካተቱበትና መሰረታዊ ክፍተት ያለበት ነው፡፡ እንደዚሁም ሕብረተሰባችን የወንጀል ጉዳዮችን የሚፈታበት የዳበሩ ባህላዊ ስርዓቶች ያሉት ቢሆንም በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርአት ህጉ ውስጥ በአግባቡ አልተካተቱም፡፡ በመሆኑም በ1954 ዓም የወጣው እና በስራ ላይ ያለው የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስነ ስርአት በዘመናዊም ሆነ በባህላዊ አግባብ የሚታዩ እድገቶችን እና ተግባሮችን አሟልቶ ያልያዘ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም ከሕገ መንግስቱ፣ ከፌደራል ስርዓቱ፣ ከአለምአቀፍ ህጎች እንዲሁም አለም አቀፍ ተቀባይት ካላቸው የዘመኑ አሰራሮች ጋር የተጣጣመ የወንጀል ሕግ ሥነ ሥርአት እና የማስረጃ ህግ ማውጣት በማስፈለጉ ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ አዋጅ ላይ በዝርዝር ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

2. በመቀጠልም ምክር ቤቱ የግልግል ዳኝነትን እና የዕርቅ አሰራር ስርዓትን ለመደንገግ በቀረበ ረቂቅ አዋጅ ላይ ተወያይቷል፡፡ የግልግል ዳኝነትና የእርቅ አሰራር ስርአት መዘርጋቱ ያለመግባባት መፍቻ አማራጮችን በማስፋት ፍትህ የማግኘት መብትን ለማሟላት አጋዥ ከመሆኑም በተጨማሪ በተለይም የኢንቨስትመንትና ንግድ ነክ አለመግባባቶችን ለመፍታት እና ለዘርፉ እድገትም አስተዋፅኦው የላቀ ነው፡፡ በሌላም በኩል በሀገራችን የግጭት መፍቻ ዘዴ ተደርገው በባሕል ውስጥ ሰፊ እውቅና ከተሰጣቸው የግጭት መፍቻ ዘዴዎች አንዱ ዕርቅ በመሆኑ የህግ እውቅና መስጠት ተገቢ ነው፡፡ የግልግል ዳኝነት እና ዕርቅ የተዋዋይ ወገኖችን ወጪ በመቀነስ፣ ሚስጢርን በመጠበቅ፣ እና ቀላልና ለተዋዋይ ወገኖች ነፃነት ያለው ሥነ ሥርዐት ለመጠቀም በመፍቀድ የተቀላጠፈ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል በመሆኑ ሂደቱ የሚመራበትንና ውሳኔዎቹም የሚፈጸምበትን አጠቃላይ ማዕቀፍ መደንገግ አስፈላጊ በመሆኑ ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ አዋጅ ላይ ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

3. በመጨረሻም ምክር ቤቱ የአክሬዲቴሽን አገልግሎት ክፍያ ረቂቅ ደንብ ላይ ተወያይቷል፡፡ ዓለም አቀፍ መመዘኛዎችን የሚያሟላ ብሔራዊ የአክሬዲቴሽን ሥርዓትን በመገንባት የአገራችን ምርቶችና አገልግሎቶች በአገር ውስጥ ገበያና በዓለም አቀፍ ገበያ ተቀባይነት ያላቸውና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ እንዲሁም በአገር ውስጥ የሚሰጡ የተስማሚነት ምዘና አገልግሎቶች ዓለም አቀፍ እውቅና እንዲያገኙ ለማስቻል ጥራት ያለው የአክሬዲቴሽን አገልግሎት በአገራችን ተግባራዊ ማድረግ ወሳኝ ነው፡፡ ለዚህም የኢትዮጵያ ብሔራዊ አክሬዲቴሽን ጽ/ቤት ለሚሰጣቸው የተለያዩ የአክሬዲቴሽን አገልግሎቶች ከጊዜው ጋር የሚሄድ የአገልክሎት የክፍያ ማሻሻያ ረቂቅ ደንብ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ ደንብ ላይ በዝርዝር ከተወያየ በኋላ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣና በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

//